*ፓኖራማ ቁጥር 51*

## *የትዝብት አድማስ*

## *የዛሬይቱ ኢትዮጵያ የትምሕርት ተቋማት*

*ኅዳር 21 ቀን 2001 ዓም*

*ምናልባት በአንድ እጅ ጣቶች ሊቆጠሩ ከሚችሉት ሀገሮች በስተቀር÷ በአፍሪካ ውስጥ ከአምሳ ዓመታት በፊት ዩኒቨርሲቲና የከፍተኛ ትምሕርት ተቋማት የነበራት ኢትዮጵያ ብቻ እንደነበረች የሚካድ አልነበረም። እንዲያውም ከራሷ አልፋ ተርፋ ገና በቅኝ ግዛት የነበሩትን ሀገሮች ተማሪዎችንም ጭምር ሳይቀር የነፃ ትምሕርት ዕድል በመስጠት አሰልጥና ትልክ እንደነበረ ሁሉም የሚያውቀው ነው። በጊዜው የነበሩት ልዩ ልዩ የትምሕርት ተቋማትም የሀገሪቱን የዕድገትና የልማት ፍላጎት ሊያሟሉ ይችላሉ የተባሉትን የሰው ኃይላት እያሠለጠኑ በማውጣት ሲጫወትቱ የነበረው ሚና ዛሬ እንደ ፋና ወጊ ሊቆጠር ይችላል። የትምህርት ተቋማቱ ሲሰጡት የነበረው ትምሕርት÷ በጥራቱም ይሁን በዓይነቱ በአፍሪካ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዳልነበረው በየሙያቸው እየሰለጠኑ የወጡት ሁሉ ሲያበረክቱት የነበረው የሥራ ውጤት ታሪካዊ ምስክርነቱን አይነፍግም። ሀገርን ከድህነት÷ ከራሀብና ችግር÷ ከኋላ ቀርነት ለማውጣት ከተፈለገ መቸም የሠለጠነ የሰው ኃይል በግንባር ቀደም ከሚጠቀሱት ዋና ዋና ጉዳዮች አንዱ እንደሆነ የሚካድ አይደልም። በመሆኑም ከከፍተኛ የትምህርት መስጫ ማዕከሎች ሰልጥነው የወጡት ምሁራን÷ በህክምና÷ በርሻ÷ በህግ÷ በመሀዲስነት÷ በቴክኒክና በልዩ ልዩ ሙያ ውስጥ በመሰማራት ሲያገለግሉ እንደነበር ዛሬ አስተዋይ ኅሊና ያለው ሁሉ የሚያስታውሰው ነው። የጀት አይሮፕላኖችን በማብረር በአፍሪካ ደረጃ ቀደምትነትን በመያዝ አድናቆትን ያተረፉት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፓይለቶች የሰለጠኑት÷ በሀገራቸው የትምህርት ተቋም ነው። ይህንን እንዲያው እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ተፈልጎ ነው እንጅ÷ በተለያዩ የሞያ መስኮች ተሰማርተው የነበሩት ባለሙያዎች÷ ለሀገራቸው ያበረከቱት አገልግሎት ግምቱን መተመን የሚቻል አልነበረም። የእኛ ነገር መቸም በነበር ብቻ መነገር ሆኖ ቀርቷል።*

*የኢትዮጵያ የትምህርት ተቋማት የተመሠረቱትና ባለሙያዎቹም የሠለጠኑት÷ ደሀው ገበሬና ሠራተኛ በከፈለው ግብር ነበር። የኢትዮጵያ ግብር ከፋይ÷ በተለይም ገበሬውና ሠራተኛው÷ ይህንን የሚያደርገው/ያደረገው÷ ከዕለት ጉርሱ ከዓመት ልብሱ እየተነጠቀ ነበር/ ነውም። የድሀው ገበሬና የሠራተኛው ዓላማ÷ ተምረው ያሳልፉልኛል የሚል ነበር። አሁንም ያው ነው። የትምህርትም ዓይነተኛ ዓላማና ግብ ያው የሰውን ልጅ ኑሮና ሕይወት ወደ መልካም/ ወደ ተሻለ ሁኔታ መለወጥ ነበር። የኢትዮጵያ ገበሬ የኑሮ ሁኔታ*

ተለውጧል ባይባልም፥ ከአፉ እየተነጠቀ ለትምህርት ፕሮግራም የዋለው ገንዘብ ደግሞ ሁሉም እንዲያው በከንቱ ፈሰሷል ማለት ያስቸግራል፡፡ መንገድ ተሰርቶለት፣ መብራት ገብቶለት፣ ንፁህ ውሃ ቀርቦለት፥ በየአቅራቢያው ትምህርት ቤት ተከፍቶለት፥ የጤና ጣቢያዎች ተቋቁመውለት የገጠሪቱን ኢትዮጵያ ነዋሪ ዜጋ ህይወት ለመለወጥ ተችሏል ማለት ግን አንችልም፡፡ ውሃ በጀርባዋ ተሸክማ ብዙ ርቀት የምትሄደውን የገጠር ሴት መከራና ስቃይ ማን ሊዘነጋው ይችላል? እራሳችንን ካላታልልን በስተቀር፡፡

የትምህርት መሳፋፋትና የሠለጠነ የሰው ኃይል ማምረት ተቀዳሚና ዓይነተኛ ዓላማ፥ የሀገሪቱን ነዋሪ ኑሮ መለወጥና የተሻለ ሕይወት እንዲመራ መድረግ መሆኑ ባይካድም፥ የሀገራችን የገጠር ነዋሪ ግን አሁንም ያው በመካከለኛው ክፍለ-ዘመን ከነበረው ህይወት ተለይቶ የሚታይ አለሆነም፡፡ የኢትዮጵያ ጉዳይ በሁለንተናዊ ገፅታው አድሮ ጥጃ ከመሆን አላላፈም፡፡ የትምህርት ተቋማት ብዛት፥ የተማረው ዜጋ መበርከት ዋናው ጥቅሙ የአንድን ሀገር ዜጋ የኑሮ ደረጃ ከፍ ማድረግ ነበር ፡፡ ይህ በሀገራችን እስካሁን አለተከሰተም፡፡ ምንም እንኳን በሀገራችን ለአለፉት ሠላሳ ስድስት ዓመታት ሁለት የተለያዩ ፈጣንና እጅግ ፅንፈኛ የሆኑ እንዲሁም፥ አንዱ ሌላውን የሚፃረር ለውጦች ቢካሄዱም፥ በኢትዮጵያ ብሄራዊ የኢኮኖሚ ጠቅላላ ድምር ውጤትም ሆነ፥ የዜጎቿ የነፍስ-ወከፍ ገቢ ምንም ያህል ያስገኘው ለውጥ የለም፡፡ በሽታው፥ ረሀቡ፥ ድኅነቱ፥ የሰላም ፅጦቱ፥ አለመረጋጋቱ፥ የትምህርቱ ደረጃ ዝቅ ማለቱ ወዘተ.. ከዛሬ ሠላሳ ስድስት ዓመት በፊት ከነበረው ሁኔታ በሚያስከፋና በሚያስደነግጥ መልኩ ብሷል እንጅ አልተሻሻለም፡፡ በኢትዮጵያ የተፈራረቁት የደርግ ሶሻሊዝም ይሁን የወያኔ የጎሳ ፌደሬሽን ያስከተሉትን ብሄራዊ ጥፋት ሕዝቡ ስለሚያውቀው መዘርዘር የሚያስፈልገን አይደለም፡፡

ለአንድ ሀገር ዕድገትና ሥልጣኔ የሚያስፈልጉ ሦስት ዓበይት ጉዳዮች፥ ማለት የማኅበራዊ ስር ነቀል ለውጥ፥ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና የሰለጠነ የሰው ኃይል ጉልበት ተገጣጥመው መገኘት መሆኑ ሁሉም ይስማማበታል፡፡ እነኝህ መሠረታዊ ጉዳዮች ከተሳኩ፥ በዕርግጥ የተሳካና ለሀገር ዕድገት የሚጠቅም ብሔራዊ የትምህርት ፖሊሲ ማውጣት የሚቸግር አይሆንም፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው ግን፥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና ሀገርና ሕዝብ ወዳድ የሆኑ መሪዎች፥ ሥልጣነ - መንግሥት ሲረከቡ ብቻ ነው፡፡ እንደ አንበሳ የተራበው፥ እንደ ተኩላ የተጠማው የኢትዮጵያ ሕዝብ፥ በህይወቱ እንኝህን ጉዳዮች ለማግኘት አልተደለም፡፡ ዕድሉን ለመወሰን ኑሮዉን ለማሳካት የሚችለው፥ ግን መልካም ዕድሉን እንዳያገኝ አንቆ የያዘውን አምባገነን ሥርዓት ሲያስወግድ ብቻ እንደሆነ የሚያከራክር አይደልም፡፡ አምባገነኖችን ለማስወገድ ደግሞ ሀገር ወዳድ ምሁራንና ለዲሞክራሲያ ሥርዓት የሚታገሉ ድርጅቶች የሀገሪቱን ሁኔታ በሚገባ ተረድተው፥ የትግሉን አካሄድና አቅጣጫ በሚገባ ተረድተውና ተረዳድተው፥ ተስማምተውና ተባብረው በጋራ መስራት ሲችሉ ነው፡፡ የአንዱ መኖር ለሌላው ይጠቅማል እንጅ የሚጎዳ አልነበረም፡፡ ይህ እስካሁን ምናልባት ተሞክሮ እንደሆን እንጅ፥ ፈጽሞ ስኬታማ ሊሆን አልቻለም፡፡ ሁለቱም የሀገር ጠቃሚ ክፍሎች እስካሁን ጠቀሜታቸውን

የሚያሳዩበትን ሁኔታ ለመግለፅ ሳይችሉ ቀርተዋል። ሁለቱም ድርና ማግ ሆነው ሰርተው ቢሆን ኖሮ፥ ከሠላሳ ስድስት ዓመታት በኋላና ያ ሁሉ መሥዋዕት ተከፍሎ፥ ዛሬ ሀገራችን አሁን ባለችበት ሁኔታ በጭራሽ ባልተገኘችም ነበር። እንዲያውም ይባስ ተብሎ፥ልማቱና ዕድገቱ መምጣቱ ቀርቶ፥ እራሷ ሀገሪቱ እንኳን ዛሬ በህልውና ደረጃ በመሞትና በሽረት መካከል ትገኛለች። ይህም በመሆኑ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ፥ "ጽድቁ ቀርቶብኝ በወግ በኮነነኝ"፥ ማለትም፥ ልማቱ ቀርቶብኝ ሀገሬ በዳነችልኝ ለማለት ተገድዷል። አሳዛኝ እንቆቅልሹና እስካሁንም መፍቻ ያልተገኘለት አዚም፥ ኢትዮጵያ ሁሉንም ሳታጣ አንዱንም አለማግኘቷ ነው። ምሁሮቿም ሆኑ ዜጎቿ እንደ ባቢሎን ግንብ ሰሪዎች መስማማት፥ መደማመጥ፥ መተማመንና መተባበር አቅቷቸው፥ ውሉ እንደ ጠፋበት ድር የጠራጠርና የመተናኮል ቁራኛና ሰለባዎች ሆነዋል።

ተደጋግሞ ተደጋግሞ እንደሚነገረው ከሆነ፥ ኢትዮጵያ በተለያየ ሙያ የተካኑ የሰለጠኑና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳድርው ከፍኛውን ደረጃ የያዙ እጅግ ብዛት ያላቸው ምሁራን እንዳሉ ይታወቃል። እንደ ጨው ዘር በዓለም ዙሪያ የተበተነው ምሁር በዓይነትም፥ በጥራትም ሆነ በብዛት ሲታይ የአፍሪካን ሀገሮች በዕጥፍ ድርብርብ እንደሚያስከነዳ የሚናገሩ ሰዎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።ይህ ሁሉ የሰሠለጠነና የደለበ የሰው ኃይል የባዕድ ሀገሮችን እያገለገል እያለ፥ በአንድ በኩል ደግሞ ሀገሪቱ የመጨረሻውን የኑሮ ደረጃ ይዛ ስትገኝ፥ ይህ እንቆቅልሽ፥ አዚምና የታሪክ ምፀት ምን እንደሆነ ለመረዳት ያስቸግራል። ሀገራችን የችግሯ ገመድ ሊበጠስ ያልቻለውና መፍተሄ ማግኘቱ ቀርቶ፥ገና የችግሯን ማንነት እንኳ በጥልቀት ለመረዳት ያልተቻለበትን ምክንያት ለማወቅ ተችሏል ማለት አልተቻልም። እስከአሁን!! ቻይና ፥ደቡብ ኮሪያና ሕንድ በአርአያነት ከሚጠቀስበት አንዱ፥ በውጭ ሀገሮች ያሏቸው ምሁራን በሀገር ግንባታ ላይ የሚጫወቱት ማዕከላዊ ሚና ነው። የሚገርመው ደግሞ፥ እነዚህ ለአብነት የተጠቀሱት ሦስት ሀገሮች በአጭር ጊዜ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ የደረሱት፥ የቆየ ባህላቸውን ዕምነታቸውን፥ ታሪካቸውንና ሥነ-ምግባራቸውንም ሆነ ብሔራዊ ማንነታቸውን ሳይበርዙ እንደጠበቁ ነው። ሳይከካ ተቦካ እንደሚባለው ይትበኃል፥ እኛ ምኑንም ሳንይዘው ሀገርንና ታሪክን ሊያጠፉ በሚችል ላይ እናተኩራለን። ሀገር ጠፉ፥ ታሪክ ወደመ፥ ሊባል የሚቻለው እኮ ተተኪውን ትውልድ የአልባሌ ባህል ሰለባ ሲደረግ ነው።ታዲያ በዚህ እረገድ ወያኔ ግንባር ቀደም ሚና መጫወቱ ያለምክንያት አይደለም። ተተኪን ትውልድ መበከል ማለት፥ ነገ ኢትየዮጵያ እንደ ሀገር ዜጎቿም እንደ ሕዝብ እንዳይቀጥሉ፥ እንደይኖሩ ማድረግ ማለት ነው። የሠለጠነ ኃይል አለ ማለት በሳይንስ፥ በቴክኖሎጂና በዕደ -ጥበብ መራቀቅ ብቻ ሳይሆን፥ የሀገርን ሁለንተናዊ ችግር ተረድቶ መፍተሄ ማግኘትንም ጭምር የሚያጠቃልል ነው ። ይህ እስካሁን በሀገራችን ተከስቷል ብለን ለመናገር የምንቸገር ይመስለናል።

የምሁራን ፍለሰት የአዕምሮ ንጥፈት በሀገራችን መከሰት የጀመረው በዘመነ ደርግ መሆኑ ባያከራክርም÷በብዛት ሀገሩን እየለቀቀ እንዲሰደድ የሚደረገው ግን ፀረ-ሀገርና ፀረ- ልማት በሆነው በወያኔ ዘመነ-መርገም ነው:: የአንድን ሀገር ሕዝብ ከታላቅ ድኅነት አላቅቀው ለኢኮኖሚ ዕድገት ከሚያበቁት መካከል÷ የዚያች ሀገር የተፈጥሮ ኃብትና የአየር ጠባይ÷ የሕዝቡ ሥራ ወዳድነትና ታታሪነት÷ እንዲሁም የሰለጠነ የሰው( የ) ጉልብት ኃይል በቅድሚያ የሚጠቀሱ ናቸው:: እነኝህን ሁሉ ኢትዮጵያ የተነፈገች አይደለችም:: ያም ሆኖ ግን÷ የሰለጠነው የሰው ኃይል በልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ የሚጠበቅበትን ሁሉ አሟልቷል ግዴታውን ተወጥቷል ማለት አንችልም:: የፖሊቲካው ሥርዓት ያስከተለው ተፅዕኖና አንደምታ ብሎም ያመጠው አሉታዊ ውጤት በቀላሉ የሚገመት ሆኖ አልተገኘም:: የተማረው የሰው ኃይል አገሩንና ያስተማረውንም ሕዝብ ለማገልገል ለአልቻለበት ሁኔታ በቂ ምክንያትና ማጠየቂያ አለው ለማለት ቢቻልም÷ እናም ደግሞ÷ ሕዝቡን ለማገልገል ባለመቻሉ የሞራልና የመንፈስ ቆርቋሬ ሊኖረው ቢችልም፤ ዞሮ ዞሮ ተጎጅዎቹ ሀገሪቱና ዜቾቿ ናቸው:: በተለይም የገጠሩ ነዋሪ! ምሁሩ ቢሰደድም÷ በግል ደረጃ ሊጎዳ የሚችል የኅብረሰብ ክፍል አይደለም:: ሌላው ቢቀር በሀገሩ ውስጥ ለመኖር ባይችልም እንኳ በመላው ዓለም ተሰድዶ በሙያው ሠርቶ የመኖር ዕድሉ የመነመነ አይደለም::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ሞልቶ- ተርፎት÷ ነገር ግን አንዱንም ሳያገኝ የበይ ተመልካች በመሆን በችግር ይማቅቃል:: ሁሉንም ነገር ባያጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንዳችም ነገር ባለማግኘቱ ÷ “ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ” እየለ ይኖራል:: በዕርግጥ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ችግሮች ለመፍታት መሁሩ የሚጫወተው ሚና ወሳኝነት ቢኖረውምው÷ የዘር ፖሊቲካ ባስከተለው ሰበብ ልክ እንደማንኛውም ዜጋ ሀገሩን እየለቀቀ ለመሄድ ተገድዷል:: ይህንን ሁሉም ዜጋ ሊረዳለት ይቸላል:: ያም ሆነ ግን እንኳን ከወያኔ ተላቀቅሁ በሎ ብቻ ሀገሪቱ ያለችበትን አደገኛ ሁኔታ ለመዘንጋት ግን አይጠበቅበትም:: በዓለም የተሰራጨው ምሁርና የሠለጠነው የሰው ኃይል÷ ሀገሩን ከጥፋት ለማዳን ኃላፊነትም ግዴታም እንዳለው ማወቅ አለበት:: አስተምሮ ለዚህ ያበቃው የደሀ ገበሪና የሠረተኛም ዕዳ እንዳለበት ይገነዘበዋል:: ከአንዳንድ ገዴለሽ በስተቀር! ያስተማረውን የደሃ ገበሬና የሠራተኛው ሕዝብ ለመክፈል አብዛኛው ምሁር ማንም ሳያስታውስው እርሱ እራሱ እንደሚገነዘበው ምንም ጥርጥር የለም:: ዕዳውን ያልከፈለና አደራውን የበላ ዜጋ መሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ ባኅርይ የሚገልፅ እንዳልሆነም ሁሉም ዜጋ ይረደዋል::ምክንያቱም÷ መልካም ሥነምግባርና ባኅርይ ያለው ዜጋ ሁሉ÷ ከተተኪው ትውልድና ከታሪክ ወቀሳ ነፃ መሆንን ስለሚፈልግ ነው:: በዓላማቸው ፀንተው የሚታገሉትን ድርጅቶችንም መደገፍ÷ መርዳና ሲሳሳቱም ምሁራዊ ምክርና ተግሳፅ እንዲያቀርብባቸው ይገባል:: ይህ ደግሞ ከህሊና ወቀሳ ነፃ የወጣ ዜጋና የሞራል ሥልጣን አለኝ ብሎ በንፁህ ኅሊናው ከሚተማመን መለካም ዜጋ የሚጠበቅ ፀጋ ነው ብለን እንገምታለን:: የኅሌናው ተገዥ የሆነና አዕምሮውን ለማንም/ ለምንም የማያስገዛ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይህንን ከመፈፀም ሊያመነታ አይገበውም እንላለን:: ለመኖር ብቻ ሲባል የሚኖረው ኑሮ ደግሞ ካለመኖር

*የሚቆጠር ይመስለናል፡፡ በመኖርና ባለመኖር መካከል ያለው ልዩነት፥ በመሞትና በሕይወት በመኖር መካከል እንዳለው ልዩነት ብቻ አይደለም፡፡ በህይወት እያሉ መሞትና እየሞቱ በመኖር መካከል ያለም ልዩነት ጭምር ነው፡፡*

*የወያኔ የትምህርት ፕሮግራም፥ ቀደም ሲሉ ከነበሩት ተፈራራቂ የትምህርት ፕሮግራሞች በዓላምም ይሁን፥ በይዘት፥ በጥራትም ይሁን በዓይነት በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ በዘር ላይ የተመሠረተው የጎሳ ፌዴሬሽን በዘረጋው የክልል አወቃቀር መንስዔ፥ ብሔራዊ የትምሕርት ፕሮግራም የሚባል ነገር ዛሬ የለም፡፡ የኢትዮጵያን ህፃናት በሀገራዊ የትምሕርት ፕሮግራም ውስጥ አካትቶ ስለመላዋ ኢትዮጵያ ሀገራቸው እንዲማሩና እንዲያውቁ የሚደረገውን ዕድል ሁሉ ዘግቶባቸዋል፡፡ ይህ የዛሬው ትውልድ፥ ኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያ የሚባል ጉዳይ፥ ጉዳዩ እዳልሆነ ተደርጎ የተነገረው ይገኛል፡፡ በየክልልህ ተወስነህና ተደይንህ ደንቆር ተብሎ ተፈርዶበታል፡፡ ወያኔዎቹ፥ የኢትዮጵያን ሕዝብ፥ አደህይቶ፥ አደንቆሮ፥ ከፋፍሎና አዳክሞ ለመግዛት ያለውን ፖሊሲ ተገባራዊ ለማድረግ፥ ለነገዋ ኢትዮጵያ ሊያስብ የሚችለውን ዜጋ ማደንቆር ነው፡፡*

*የማነኛቸው ሀገር ብሔራዊ የትምሕርት ፖሊሲ ሲወጣ ሁለት ዓበይት የመሠረት ድንጋዮች መጣል ይኖርባቸዋል፡፡ አንደኛው ሥርዓተ- ትምሕርት ሲሆን፥ ሁለተኛው የመማርያ መጻሕፍት ናቸው፡፡ እነኝህ የአንድን ሀገር ብሔራዊ የትምሕርት ፖሊሲ ለመቅረፅ መዕከላዊ ሚና ይጫወታሉ ሲባል፥ የሀገሪቱን ብሔራዊ ዕሴትና ራዕይ፥ ታሪክና ባኅል፥ የፖለቲካ ፥ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ እንዲሁም የሕዝቡንም የወደፊት ብሩኅ ተስፋ የሚያንፀባርቅ የትምህርት መመሪያ መዘጋጀት አለበት ማለት ነው፡፡ ይህ በዘረኞች በምትገዛው ኢትዮጵያ ዛሬ የለም፡፡ ለምን ይህ ይሆናል ብሎም የሚገረመም ዜጋ አይኖርም፡፡ ምክንያቱም ወያኔዎቹ ስለ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም የቆሙ ባለመሆናቸው ነው፡፡ የብሔራዊ የትምሕርት ፖሊሲ የሌለው ሀገር ደግሞ፥ ከአንድ ትውልድ በኋላ ቀጣይነት ስለማይኖረው፥ ሀገሩም እንደ ሀገር፥ ትውልዱም እንደ ትውልድ የሚቀይበት ዕድሉ የመነመነ ይሆናል፡፡ ለአለፉት አስራ ስምንት ዓመታት ወያኔዎቹ ሌት ከቀን ሲሰሩት የቆዩትም፤ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር፥ ዜጎቿም እንደ ሕዝብ እንዳይኖሩ ቀስ በቀስ እንዲጠፉ ለማድረግ በመሆኑ ይህ የማጥፋት ዕቅዳቸው የሚሳካ ይመስላቸዋል፡፡ ያ ግን እንማይሆን በዕርግጠኝነት መናገር እንችላልን፡፡ ምክንያቱም የዛሬዋ ኢትዮጵያ ከኅልፈተ ወያኔ በኋላ ትንሳዔወን አግኝታ ዘለዓለማዊነቷን ስለምታረጋግጥ ነው፡፡ የትምህርት ፖሊሲያዋም ያን ጊዜ ብሔራዊ መሆኑ የማይቀር ነው፡፡*